# ዕርቁ ቀኖና ቤተክርስቲያንን የጠበቀ ካልሆነ ይቅር !!!

ምክንያቱም ቤተክርስቲያንን ይጎዳል እንጅ አይጠቅምምና ነው!!! ይሄ ጉዳይ ፈጽሞ ለድርድር የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም!!!

ወገኖቸ እግዚአብሔርን መቅደም አይቻልም!!! እምነት የጎደላቸው ሥጋውያን ተሳስተው እንዳያሳስቱን እንጠንቀቅ እንታቀብ!!!

ከቀኖና ቤተክርስቲያን ውጭ ዕርቅ ለመፈጸም መሞከር የእግዚአብሔርን ክብር ማስደፈር፣ ቤተክርስቲያንንም ማዋረድ ነውና በእጅጉ እንጠንቀቅ እንታቀብ!!!

አላዊው የወያኔ አገዛዝ ከመንበረ ፕትርክናቸው አፈናቅሎ ያሰደዳቸውንና በሰሜን አሜሪካ በስደት ያለውን ሕጋዊውን ሲኖዶስ ሀገር ቤት ካሉት የመለካውያኑ ቡድን ጋር ለማስታረቅ ከሁለቱም ወገኖች የተወከሉ አባቶች ለዘጠኝ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ድርድር ለማድረግና ዕርቅ ለመፈጸም በሰሜን አሜሪካ ድርድር መቀመጣቸው ተነግሯል፡፡

ለድርድሩ ይሄንን ያህል ቀን መያዙ ዕርቁ ሕገ ቤተክርስቲያን ወደጎን ተገፍቶ የሰጥቶ መቀበል ሥጋዊው የመደራደሪያ ስልትን ለመጠቀም ታስቦ በመሆኑ እንዳይሆን ከፍተኛ ሥጋት አጭሮብኛል፡፡

ምክንያቱም ዕርቁ ቀኖና ቤተክርስቲያንን መሠረት ያደረገ ከሆነ ሕገ ቤተክርስቲያን ይሄንን ጉዳይ ያለ አንዳች ውዝግብ ለመፍታት በሚያስችል ደረጃ ጥርት ብሎ የተቀመጠ በመሆኑ ዘጠኝ ቀናት አይደለም ዘጠኝ ሰዓታት እንኳ የሚወስድ አይደለምና ነው፡፡

እነኝህ የተላኩ ተደራዳሪዎች ሌላ የሚሉት ነገር እኮ የለም፡፡ በቃ "ቅዱስ አባታችን! በወቅቱ እኛም ለነፍሳችን ፈርተን፣ ቀኖና ቤተክርስቲያንን ጥሰን ከአገዛዙ ጋር ተባብረን አሳድደነዎታል ይቅር በሉን? ይፍቱን? ቅዱስ አባታችን! ለ 26 ዓመታት በስደት የቆየውን ሲኖዶስ ይዘው ወደ መንበረ ፕትርክናዎ ይመለሱልን? መንበረ ፕትርክናዎን ለማስረከብ ተዘጋጅተናል! ለበደላችንን ይቅር ይበሉንና ይመለሱልን ቅዱስ አባታችን? ቀኖናም ይስጡን?" ነው ማለት የሚጠበቅባቸው፡፡ ዕርቁ ቀኖና ቤተክርስቲያንን የጠበቀ ከሆነ ይሄንን ነው የሚሉት ሌላ ሊሉት የሚገባ ነገር የለም መኖርም የለበትም፡፡

ምክንያቱም ቀኖና ቤተክርስቲያን ፍጹም በማያሻማ በማያወላዳ መልኩ "ፓትርያርክ በሕይወት እያለ ፓትርያርክ አይሾምም!" ብሎ ዘግቶታልና፡፡ ፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 4 ቁጥር 68-70፡፡

"የፓትርያርክ ሥልጣን በአንድ ዘመንና በአንድ ሀገር ለ 2 ሰዎች ልትሆን አይገባም!!! በአጋጣሚ በተለያየ ምክንያት ተፈጽሞ ከተገኘ ግን መንበሩ ወይም ሥልጣኑ ቀድሞ ለተሾመው ትጽናለት!" ይላልና፡፡ ፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 4 ቁ.70

ይሄንን ቀኖና የሠሩት 318ቱ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን በጉባኤ ንቂያ ላይ በ325 ዓ.ም. በመንፈስቅዱስ ተቀኝተው የደነገጉት ቀኖና ቤተክርስቲያን ነው፡፡ ፍትሐ ነገሥት ስለተባለ ነገሥታት የደነገጉት እንዳይመስላቹህ፡፡

በመሆኑም የወያኔ አገልጋዮች ቡድን መለካውያኑ ፓትርያርክ እያሉ የሾሚቸውን የሁለቱን ተጋዳላዮች ፕትርክና ቤተክርስቲያን አታውቀውም እግዚአብሔር አይቀበለውም፡፡ እውነቱ ይሄው ነው ቤተክርስቲያን ሌላ እውነት የላትም!!!

በወቅቱ እነኝህ መለካውያኑ (ሕገ እግዚአብሔርን በመተላለፍ የባለሥልጣናትን ትዕዛዝ ፈጻሚዎች ወይም አገልጋዮች) ቅዱስ ፓትርያርኩን ከአገዛዙ ጋር ተባብረው ተፈራርመው ከመንበራቸው ሲያፈናቅሏቸው ምክንያት ያደረጉት ቅዱስነታቸውን "በጠና ታመዋልና መሥራት አይችሉም!" በማለት ነበር፡፡

ይሄ እርምጃቸው ግን ቀኖና ቤተክርስቲያንን የጣሰ ያፈረሰ፣ የእግዚአብሔርን ሕግ የተዳፈረ ነበር፡፡ ምክንያቱም እንኳን በጠና ያልታመሙትን ቢታመሙ ኖሮ እንኳ ቀኖና ቤተክርስቲያን "በኋላ የሚድን ከሆነ በሚያልፍ በሽታ ምክንያት ሹመትን ከመያዝ ሰው ሁሉ የሚከለከል አይደለም። ፍጹም ድኅነትን እስኪያገኝ ድረስ ልትጸናለት ይገባል!" ብሎ ደንግጓልና ነው፡፡ ፍ/ነ/ፍ/መ አንቀጽ 4 ቁ.78፡፡

ስለዚህ ነው እነኝህ መለካውያኑ ጥፋታቸውን አምነው ንስሐቸውን ከበደሏት ቅድስት ቤተክርስቲያን ተቀብለው ራሳቸውን ካዳኑ በኋላ ሔደው ከቅዱስነታቸው እግር ወድቀው ይቅርታ በመጠየቅ ቅዱስነታቸውን ለመመለስ ጥረት ማድረግ የግድ የሚጠበቅባቸው፡፡

ከዚህ ውጭ ፈውስ የለም!!! ከዚህ ውጭ በሆነ መንገድ ዕርቅ ለመፈጸም የሚፈልግ ካለ እሱ ቅሉፍ ነው፡፡ ይህ ከላይ በገለጽኩት መንገድ ዕርቁ መፈጸሙ ግድ የሚሆንበት ምክንያት በዚህ በደል ካዘነው ልዑል እግዚአብሔር ፈውስ፣ ይቅርታ፣ ምሕረት ማግኘት የምንችለው፣ ከስብራታችን የምንጠገነው፣ ከበደላችን የምንነጻው ይሄንን ካደረግን ብቻ ስለሆነ ነው እንጅ ቅዱስነታቸውንና አብረዋቸው ያሉትን ብፁዓን አባቶችን አሸናፊ እዚህ ያሉትን መለካውያኑን ደግሞ ተሸናፊ ለማድረግ አይደለም!!!

የቤተክርስቲያናችን ሥርዓት የንስሐን ወይም የቀኖናን አፈጻጸም በተመለከተ በደል፣ ጥፋትና ስሕተት ልቅም ብላ ሳትነገር በሸፍንፍን፣ በማለባበስ፣ በመደፋፈን እንዲሆን ፈጽሞ እንደማትፈቅድና አጥፊ ጥፋቱን ግልጥልጥ አድርጎ ሳይናገርና ሳይጸጸት ከንስሐና ቀኖና የሚገኝ ፈውስ፣ ይቅርታና ምሕረት የሚባል ነገር ጨርሶ እንደሌለ እራሳቸው መለካውያኑም ጠንቅቀው ያውቁታል፡፡ ንስሐና ዕርቅ ፈውስ የሚያስገኘው በዚህ ቀኖና ቤተክርስቲያን ባስቀመጠው መንገድ ሲሆን ብቻና ብቻ ነው፡፡ አለቀ!!!

እንግዲህ እውነቱ፣ መሆን ያለበትና እግዚአብሔርን የሚያስደስተው ይሄ ሆኖ እያለ ምን ሲደራደሩ ሊሰነብቱ እንደሆነ አላውቅም ዘጠኝ ቀናት ሙሉ የድርድር ጊዜ ተይዞ ተደራድረው ለመቋጨት አቅደው ለድርድር ተቀምጠዋል፡፡ ችግሩ ያለው እዚህ ላይ ነው እንግዲህ፡፡ እንደ ቤተክርስቲያን ልጅነቴ እዚህ ላይ አበክሬ ማሳሰብ የምፈልገው ነገር ቢኖር ዕርቁን ለእግዚአብሔር ሳይሆን ለሰው በመቅናት፣ ለቤተክርስቲያን ሳይሆን ደምስሯን ሲቆርጥና አከርካሪዋን ሲሰብር ለከረመው የጥፋት ቡድን በማድላት፣ የቤተክርስቲያንን ጥቅም ለመጠበቅ ሳይሆን የከሐዲ ምንደኞችን ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል ሕገ ቤተክርስቲያንን ወደጎን በመተው በሰጥቶ መቀበል መርሕ ዕርቅ ለመፍጠር ከተሞከረ በዚህ የዕርቅ ጉባኤ ላይ እግዚአብሔር ፈጽሞ እንደማይኖር ሁሉም ሰው እርግጠኛ ሊሆን ይችላል፡፡

ከዚህ የተላኩት ይሄንን ሊሞክሩ ቢችሉም እዚያ ሰሜን አሜሪካ ያሉቱ አባቶች ይቀበሉታል ብየ አላስብም፡፡ ይሁንና ከፍተኛ ጫና በማሳደር እንዲቀበሉት ለማድረግ ከየአቅጣጫው ጥረት መደረጉ ስለማይቀር ይህ ቤተክርስቲያንን

የሚያሳዝን፣ እግዚአብሔርን የሚያስቆጣ ድፍረት እንዳይፈጸም ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንና ምእመናን ቅርብ ክትትል እንድናደርግበት አጥብቄ ማሳሰብ እወዳለሁ፡፡

ሕዝበ ክርስቲያን ሆይ! ከላይ በገለጽኩላቹህ ምክንያት ሰውን በማያፍሩት፣ እግዚአብሔርን በማይፈሩት መለካውያን ዕርቁን ከቀኖና ቤተክርስቲያን ውጭ ለመፈጸም ሲሞከር ቢከሽፍ እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንና ምእመናን ከንፈር በመምጠጥ አዝነን ብቻ ዝም ብለን እንደማንቀመጥ ከወዲሁ ልናስጠነቅቃቸው ይገባል!!!

ሥጋቴ ያየለበት ምክንያቱ እነኚህ ከዚህ ከመለካውያኑ (የባለሥልጣናት ታዛዥ አገልጋዮች) ቡድን ለድርድር የተላኩቱ አባቶች ከዚህ ቀደም በተለያዩ መድረኮች ሲናገሩ እንደተደመጡት እነሱ እራሳቸው ለነፍሳቸው ፈርተው፣ የክርስቶስን አደራ በልተው ቤተክርስቲያንን ወያኔ "አከርካሪዋን ሰበርኩት!" ብሎ እስኪፎክር ድረስ ቤተክርስቲያንን ለወያኔ መጫወቻ መቀለጃነት አሳልፈው የሰጡ፣ በፓትርያርኩ ስደት እጃቸው በቀጥታ ያለበት ሆነው እያለ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያን "ፈተና ቢደርስባቸውም እዚሁ መከራ መቀበል፣ ሠማዕት መሆን ነበረባቸው እንጅ መንጋውን በትነው መሸሽ አልነበረባቸውም!" በማለት "እኛ ምን አፍ አለን?" ሳይሉ እግዚአብሔርን ሳይፈሩ፣ ሰውን ሳያፍሩ፣ "ይሄንን ለማለት እኛ የሞራል (የቅስም) ብቃቱ አለን ወይ?" ሳይሉ ፓትርያርኩን ሲከሱ ሲወነጅሉ የቆዩ መሆናቸው ነው፡፡ ታዲያ እነኚህ ሰዎች ከእውነት የራቁ፣ እራሳቸውን ለእውነት ያሳመጹ ሆነው እንዴት ሆኖ ነው ለዕርቅ ያበቃሉ ተብሎ ተስፋ የሚደረገው???

ለማንኛውም የመለካውያኑ ቡድን ለማሳሳት የሚጠቅሷቸውን የቀኖና ድንጋጌዎች እየጠቀስን እንተችና እንቋጭ፡፡ መለካውያኑ ምን ይላሉ፦

"ሊቃ ጳጳስ፣ ቆሞስ፣ ኤጲስ ቆጶስ ከተሾመና እሊህን መዓርጋት ከተቀበለ በኋላ አንዲት ዕለት ወይም አንዲት ሰዓትም ቢሆን ቤተ ክርስቲያንን ያላገለገለ፣ ቀጥሎም የተሾመበትን አገር ጥሎ የሸሸ ቢኖር እሽ ብሎ ወደ ቦታው እስኪመለስ ድረስ የአገሩ ሰዎች ይማልዱት። አልመለስም ቢል ሊኖር ከሄደበት አገርና ከምእመናን ጉባኤ ይለይ!" ፍ/ነ/ፍ/መ አንቀጽ 4 ቁ. 180 የሚለውን ሳያፍሩ ይጠቅሱና ለይተናል ይላሉ፡፡

ነገር ግን ቅዱስነታቸውና አብረዋቸው ያሉት ብፁዓን አባቶች የሔዱት በግል ምክንያታቸው ነው እንዴ??? እንመለስ ቢሉ መመለስ ይችላሉ እንዴ??? እንኳንና እነሱን አቦይ ስብሐት ዕርቁን እንድታከናውኑ የተመደባቹህትን ምን ነበር ብሎ ያስጠነቀቃቹህ??? "እርቅ ምናምን የሚሉትን ቄሶች እንሰቅላቸዋለን!" አይደለም ወይ ብሎ የነበረው??? ለዕርቅ ተወክለው የመጡትን ወዲያው አይደለም ወይ አፍኖ ከሀገር ያባረራቸው??? ስለዚህም የተጠቀሰው አንቀጽ አግባብነት የሌለው አንቀጽ ነው፡፡ አንቀጹ የሚመለከተው በገዛ ፈቃዱ ያለማንም አስገዳጅነትና አስገዳጅ ምክንያት በግል ምክንያቱ ለሔደ ለራቀ ካህን ነው፡፡

ለዚህም ነው "ኤጲስ ቆጶሳት ከሀገረ ስብከታቸው ወደ ሌላ አገር ቢሔዱ ከስድስት ወር የበለጠ አይኑሩ። ችግር ሳይገጥማቸው ሊቀ ጳጳሱም ሳይፈቅድላቸው ከዚህ የበለጠ ቢኖሩ ወይም ሀገረ ስብከታቸውን ትተው በሌላ አገር በዓለ ትንሣኤን ቢያከብሩ ከሹመታቸው ይሻሩ!" ፍ/ነ/ፍ/መ አንቀጽ 4 ቁ. 206 በማለት ችግር ካጋጠማቸው አንቀጹ እንደማይመለከታቸው የገለጸው፡፡

መለካውያኑ ሌላም የሚሉት ነገር አላቸው፡፡ ምንም እንኳ ቅዱስ አባታችንን ከአገዛዙ ጋር ተባብረው እንዲሰደዱ ያደረጓቸው እነሱው ቢሆኑም ምን ይላሉ "መንጋውን ጥለው ተሰደዋልና አናውቃቸውም!" ይላሉ፡፡ መሰደዳቸውንም እንደክህደት አድርገው ያወራሉ፡፡ ነገር ግን በአስገዳጅ ሁኔታ የሚከሰት ስደትን ከቤተክርስቲያን አስተምህሮ አንጻር ያየነው

እንደሆነ መሰደድም ሠማዕትነት መሆኑን ቤተክርስቲያን ትናገራለች ታስተምራለችና ይሄ የመለካውያኑ ምክንያት ውኃ የሚቋጥር አይደለም፡፡

ጌታም በወንጌሉ ማቴ. 10፣ 1-42 ላይ ሐዋርያትን ጠርቶ ወደ ዓለም ሲልካቸው አጠቃላይ መመሪያ በሰጠበት ትዕዛዙ ላይ "...በአንዲቱ ከተማም መከራ ቢያሳዩዋቹህ ወደ ሌላይቱ ሽሹ!" ማቴ. 10፣23 ፡፡ ብሏቸዋልና በሐዋርያት እግር የተተኩት ቅዱስነታቸውም ወያኔ መከራ ሲያጸናባቸው በመሰደዳቸው የጌታን ትዕዛዝ ፈጸሙ እንጅ በመሰደዳቸው የፈጸሙት ጥፋት የጣሱት ቀኖና የለም፡፡

በቤተክርስቲያን ታሪክም ትንታጉ አባት ቅዱስ አትናቴዎስና ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በአላውያን ነገሥታት ጫና ምክንያት መንበራቸውን ለቀው እንዲሰደዱ ከተደረጉ ቅዱሳን አባቶች ውስጥ ናቸው፡፡ ታዲያ ግን ቅድስት ቤተክርስቲያን መንጋቸውን ጥለው ተሰደዋልና ጥፋተኞች ናቸው አላለችም፡፡ ሠማዕታት ብላ ገድላቸውን ጽፋ ዘከረቻቸው እንጅ፡፡

በመሆኑም በትክክል ዕርቁ ከተፈለገ፣ ዕርቁም ቀደም ሲል በተፈጸመው ግፍ ምክንያት ያዘነውን እግዚአብሔር በሚያስደስት፣ ቤተክርስቲያንን በሚጠቅም መልኩ ለማድረግ ከተፈለገ መፈጸም ያለበት ንስሐን በማስቀደም ቀኖና ቤተክርስቲያንን በጠበቀ መልኩ ነው መፈጸም ያለበት፡፡ ከዚህ ውጭ ሌላ ምንም አማራጭ የለም!!!

ከዚህ ቀደም ለማድረግ እንደተሞከረው ማለትም ይገርማቹሃል ምዕመናን ከዚህ ቀደም በአባ ጳውሎስ ዘመን በተደረጉ የዕርቅ ድርድሮች ምን ለማድረግ ተሞክሮ ነበረ መሰላቹህ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በዓት ተሰጥቷቸው በበዓታቸው ፓትርያርክ እየተባሉ ሊኖሩ፣ የአባ ጳውሎስ ጥትርክናም ሳይሻር እሳቸውም ፓትርያርክ እየተባሉ የቤተክርስቲያኗ የአሥተዳደር ሥራው በኒሁ ከቀኖና ቤተክርስቲያን ውጭ በተሾሙት አባ ጳውሎስ እንዲሠራ ከላይ የጠቀስኩላቹህን ሁለት ፓትርያርክ እንዳይኖር የሚከለክለውን ቀኖና ቤተክርስቲያን በመጣስ፣ በመሻር፣ በመተላለፍ ዕርቅ ተፈጸመ ተብሎ ቅዱስ ፓትርያርኩን ወደ ሀገርቤት ለማስገባት ዝግጅት ተጀምሮ ነበር፡፡

ቅዱስ ፓትርያርኩ አቡነ መርቆሬዎስም አንሰጥዎትም የተባሉትን የአሥተዳደሩን ሥራ ስለማይፈልጉላቸውና በአርምሞ ያሉ፣ ዕድሜያቸውን በሱባኤ እየገፉ ያሉ ቅዱስ አባት በመሆናቸው፣ ሀገራቸውን ስለናፈቁና ወደ ሀገራቸው ገብተው በብሕትውና በበዓት ተወስነው ስለ ሀገር፣ ስለ ቤተክርስቲያን፣ ስለ ምእመናን ሰላም፣ ደኅንነትና መጠበቅ እየጸለዩ እየተማጸኑ ዕለተ እረፍታቸውን መጠበቅ ስለሚፈልጉ ተስማምተው ነበር፡፡

ነገር ግን ዕርቁ ቀኖና ቤተክርስቲያንን የጣሰ የሻረ ስለነበር እግዚአብሔር ተቆጥቶ ለሥልጣንና ለጥቅም ሲሉ ቀኖና ቤተክርስቲያን ተጥሶ ተሽሮ ዕርቁ እንዲፈጸም የፈለጉትንና ያደረጉትን አቦይ ጳውሎስን ቀሰፈና አሰናበታቸው፡፡

ይሄ ምን ማለት እንደሆነ ፈጽሞ ያልገባቸውና የማይገባቸው እንዲገባቸውም የማይፈልጉት መለካውያኑ እግዚአብሔር የፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም ቅዱስ ፓትርያርኩን አምጥቶ በመንበራቸው ላይ እንደማስቀመጥ እግዚአብሔርን ትተው ለወያኔ ታዘዙና እንደገና ሁለተኛ ስሕተት በመፈጸም ፓትርያርክ ሾምን ብለው አባ ማትያስን አስቀመጡ፡፡ አየ አለመታደላቸው እናንተየ!!!

አሁንም ጥረታቸው በአባ ጳውሎስ ጊዜ የሞከሩትን ዓይነት ቀኖና ቤተክርስቲያንን የሚጻረር ስምምነት ለመፈጸም አባ ማትያስን እንደ ፓትርያርክ እንቁጠራቸውና ሁለቱንም ፓትርያርክ እያሉ በመጥራት አሥተዳደሩን ለአቦይ ማትያስና ለቡድናቸው ማለትም ወያኔነታቸውን መከታ አድርገው ቤተክርስቲያንን እንዳሻቸው ሲዘርፉ፣ ሲመዘብሩ፣ ግፍ ሲፈጽሙ፣ ቤተክርስቲያንን ሲሰብሩ፣ ደም ስሯን ሲቆርጡ፣ ካህናትን ምእመናንን ሲያስመርሩ ለኖሩት በስራቸው ላሉ የወያኔ ታጋዮች እንዲሁም ቅጥረኞች በመስጠት ቅዱስ ፓትርያርኩን (ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን) ደግሞ በበዓት ተወስነው

እንዲኖሩ ለማድረግ ከሆነ ድርድሩን ሲያደረጉ ያሰቡት እውነቱን ነው የምላቹህ ለማየት ያብቃቹህ አቦይ ማትያስም እንደ አቦይ ጳውሎስ ይቀሰፋሉ!!!

አቦይ ማትያስ ብቻም ሳይሆኑ እግዚአብሔርን ላለመስማት ጆሯቸውን ከደፈኑት፣ ልባቸውን ካደነደኑት ከመለካውያኑ የወያኔ አገልጋዮች ጳጳሳት ተብየዎችም ውስጥ ቀንደኛ ቀንደኛው ይቀሰፋል!!! እግዚአብሔርን ባዘነበትና በተቆጣበት ነገር ሁለተኛ ማሳዘንና ማስቆጣት ለበረታ ለባሰ ለከፋ ቅጣት ይዳርጋልና፡፡ እውነት ግን እነኝህ ሰዎች ይሄንን ስሕተት በድጋሜ ለመፈጸም ከሆነ እዚያ ሔደው እንደራደር እያሉ ያሉት በእውነት ነው የምላቹህ ምን ያህል የማያስተውሉ መሆናቸውንና ልበ ደንዳናነታቸውን ለመግለጽ ቃላት ያጥረኛል፡፡

እባካቹህ የንስሐ ሕይዎት እንደሰማይ የራቃቹህ፣ ጸጸት የሚባል ያልፈጠረባቹህ፣ በቤተክርስቲያን ላይ በደልና ግፍ መፈጸም የማይሰለቻቹህ ልበ ደንዳና መለካውያን ጳጳሳት ተብየዎች ሆይ! እግዚአብሔርን በድጋሜ እንዲህ አስቆጥታቹህት ከመቀሰፋቹህ በፊት እባካቹህ ለራሳቹህ ብትሉ ታረሙ???

እውነት የቤተክርስቲያን መታመስ የሚያሳዝናቹህ፣ ዕርቅ መፈጸም እንዳለበት የምታምኑ ከሆነ ዕርቁ ቀኖና ቤተክርስቲያንን ብቻ በጠበቀ መልኩ እንዲፈጸም ፍቀዱ አድርጉም???

እባካቹህ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንና ምእመናን እነዚህ እርመቢሶች ዕርቁን ከቀኖና ቤተክርስቲያን ውጭ ለመፈጸም እንዳይሞክሩና እግዚአብሔርን እንዳያስቆጡብን ለቅስፈቱ ለቁጣውም እንዳንዳረግ አጥብቃቹህ ጸልዩ ጸልዩ ጸልዩ!!!

ከአምስት ዓመታት በፊት ይሄ ከቀኖና ቤተክርስቲያን ውጭ የሆነው ዕርቅ ይካሔድ በነበረበት ጊዜ መጽሔቶች ላይ ከጻፍኳቸው ጽሑፎች ሁለቱን ልጋብዛቹህና ልቋጭ፡-

አንዱ "ጉባኤ ኬልቄዶን ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በመልካም አርአያነት ሊወሰድ ይገባልን?" በሚል ርእስ የተጻፈ ሲሆን ጽሑፉን ከመጽሔት ገልብጠው ድረገጽ ላይ የጫኑት ሰዎች ጽሑፉን ሲገለብጡ ለምሳሌ መለካዊ የሚለውን መለኮታዊ እያሉ በመጻፍ የቃላት ስሕተቶችን የፈጸሙ መሆኑ ግንዛቤ ይወሰድበትና እነሆ ጽሑፉ፡-

https://www.google.com/url?q=https://addis12.wordpress.com/2013/01/18/%25E1%258C%2589%25E1%2589%25A3%25E1%258A%25A4-%25E1%258A%25AC%25E1%2588%258D%25E1%2589%2584%25E1%258B%25B6%25E1%258A%2595-%25E1%2588%2588%25E1%258A%25A2%25E1%2589%25B5%25E1%258B%25AE%25E1%258C%25B5%25E1%258B%25AB-%25E1%2589%25A4%25E1%2589%25B0%25E1%258A%25AD%25E1%2588%25AD%25E1%2588%25B5%25E1%2589%25B2%25E1%258B%25AB/&sa=U&ved=0ahUKEwjUwPSdqq3cAhUJyaQKHTdeAJkQFggOMAE&usg=AOvVaw10_rhxOdhDG9q6na18ZN3B

ሌላኛው ደግሞ ወያኔ አቦይ ማትያስን ሊያሾም ሽርጉድ በሚልበት ጊዜ "በሕግ አምላክ 5 ሳይባል 6 አይባልም!!" የሚል ርእስ የተጻፈ ሲሆን ድረገጽ ላይ የተጫነው ግን የዛሬ አራት ዓመት እንደገና "ሲኖዶስ ይሰደዳል አይሰደድም?" የሚል ክርክር ባስነሡ ጊዜ ነው እነሆ ጽሑፉ፡-https://www.google.com/url?q=http://ethioforum.org/amharic/%25E1%2589%25A0%25E1%2588%2595%25E1%258C%258D-%25E1%258A

%25A0%25E1%2588%259D%25E1%2588%258B%25E1%258A%25AD-5-
%25E1%2588%25B3%25E1%258B%25AD%25E1%2589%25A3%25E1%2588%258D-
6-%25E1%258A%25A0%25E1%258B%25AD
%25E1%2589%25A3%25E1%2588%258D
%25E1%2588%259D/&sa=U&ved=0ahUKEwiBn52H6KvcAhUHCuwKHTyyB7kQFggLMA
A&usg=AOvVaw3IgAwS3cZecQy6zD4e1__s

ልዑል እግዚአብሔር በምሕረቱ ይጎብኘን፣ በቸርነቱ ያስበን!!! አሜን!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com